20ኛ አመት ቁጥር 15

20th Year No. 15

ባህር ዳር መጋቢት 25 ቀን 2007 ዓ.ም

Bahir Dar; 3rd Dec, 2011

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ዝክረ-ሕግ

14th Year No 16

ZIKRE-HIG
OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር **48.30** **Price Birr**	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ **312** **P.o. Box**

ማውጫ	CONTENTS
ደንብ ቁጥር **131/2007** ዓ.ም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የህንፃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	**Regulation No.** 131/2015 The Amhara National Regional State Building Works Construction Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation
ደንብ ቁጥር **131/2007** ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የህንፃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	**Regulation No.** 131/2015 A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE BUILDING WORKS CONSTRUCTION ENTERPRISE IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

በክልሉ ውስጥ የሚታዩትን የኮንስትራክሽን ዘርፍ ክፍተቶች በመለየትና በመሙላት የዘርፉን ዘላቂ ዕድገት በማረጋገጡ ረገድ የሚደግፍ ተቋም መመስረት በማስፈለጉ፣

WHEREAS, it is necessary to establish an institution that would be able to render support with regard to the realization of sustainable development of the sector by having identified and filled the gaps prevailing in the construction sector of the Region;

በክልሉ መንግስት ገንዘብ የሚካሄዱ ግንባታዎች ጊዜ እና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ በጥራት ተገንብተው በወቅቱ እንዲጠናቀቁና ለሚፈለገው ተግባር እንዲደርሱ ማድረግ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS, it has been found appropriate to see to it that those constructions financed by the Regional Government are carried out in a desired quality and completed promptly in a cost effective manner and thereby readily available for the required activity thereof;

በክልሉ ውስጥ ለሚከናወኑት ማናቸውም የልማት ሥራዎች ተፈላጊ የኮንስትራክሽን ግብአቶችን በማምረትም ሆነ ማሽነሪዎችን ከውጭ በማስገባት የዘርፉን የግብአት ዕጥረት ማቃለልና ገበያውን ማረጋጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

WHEREAS, it has been found necessary to alleviate the shortage of input prevailing in the sector and stabilize the market by producing construction inputs as well as importing machineries needed for any developmental activities carried out in the Regional State;

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ /7/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, pursuant to the powers vested in it under the provisions of Art. 58 sub-Art. (7) of the Revised National Regional Constitution, hereby issues this Regulation.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የህንፃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 131/2007 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ህንፃ" ማለት ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ ወይም ለሌላ ለማናቸውም አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው፤
2. "የህንፃ ግንባታ" ማለት ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ ወይም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታዎችን መስራት ሲሆን ለህንጻው የሚያስፈልጉ ወይም ከህንጻው ጋር የተያያዙ የመዳረሻ መንገዶች ግንባታን ይጨምራል፤
3. "ወጭ ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎች" ማለት ህንፃዎች በዝቅተኛ ወጭ እንዲገነቡ ለማድረግ ይቻል ዘንድ በስራ ላይ የሚውሉ ዲዛይኖችን፣ ግብአቶችንና የግንባታ ሂደቶችን ያጠቃልላል፤

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This regulation may be cited as "the Building Works Construction Enterprise Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 131 /2015".

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this regulation:-

1. **"Building"** shall mean a permanent or provisional structure used for dwelling, office, manufacturing or any other service thereof;
2. **"Constructing Building"** shall mean the activity of constructing a building to be used for dwelling, office, manufacturing or for any other purpose and includes the construction of access roads necessary for such building or connected therewith;
3. **"Low-cost Technologies"** shall include those designs, inputs and construction processes put to use so

4. **"አግሮስቶን"** ማለት የግብርና ተረፈ ምርቶችን እንዲሁም አያያዥና ጥንካሬ ሰጭ ኬሚካሎች ተቀላቅለው በተፈለገው ቅርፅ እየተዘጋጁ የሚወጡትን ምርቶች ይገልፃል።

4. **"Agro-stone"** shall describe those outputs to be manufactured in a process through which agricultural byproducts as well as glutinous and strengthening chemicals are mixed together and prepared in a desired shape.

ክፍል ሁለት

ስለ ድርጅቱ መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ አላማና አወቃቀር

PART TWO

ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY, OBJECTIVE AND STRUCTURE

3. ስለ ድርጅቱ መቋቋምና ተጠሪነት

3. Establishment and Accountability of the Enterprise

1. በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የህንፃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

1. There is hereby established, the Amhara National Regional State Building Works Construction Enterprise /hereinafter referred to as **"the Enterprise"**/ having become the public enterprise of the Regional Government with its own autonomy and legal personality as per this Regulation.

2. ድርጅቱ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ሆኖ ተጠሪነቱ ለርዕሰ

2. The Enterprise shall, having been

መስ/ጽ/ቤት ይሆናል።

established for an indefinite period of time, be accountable to the Office of the Head of the Regional Government.

4. መነሻ ካፒታል

ድርጅቱ የተቋቋመበት መነሻ ካፒታል በጠቅላላው ብር 500,000,000.00 /አምስት መቶ ሚሊዮን ብር/ ሲሆን ከዚሁ ውስጥ ብር 200,000,000.00 /ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር/ የሚሆነው በጥሬ ገንዘብ እና ብር 300,000,000.00 /ሦስት መቶ ሚሊዮን ብር/ የሚሆነው ደግሞ በአይነት ተከፍሏል።

4. Initial Capital

The initial capital establishing the Enterprise amounts to a total sum of Birr 500,000,000.00 /five hundred million Birr/, out of which Birr 200,000,000.00 /two hundred million Birr/ has been paid up in cash, whereas Birr 300,000,000.00 /three hundred million Birr/ in kind.

5. የኃላፊነት ወሰን

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ሀብት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

5. Limitation of Liability

The Enterprise may not be held liable in excess of its total assets.

6. የድርጅቱ ዓላማዎች

ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

6. Objectives of the Enterprise

The Enterprise shall, pursuant to this Regulation, have the following objectives:-

1. የህንፃ ሥራዎችን በማከናወንና ለክልሉና ከክልሉ ውጭ ላሉ አጐራባች ክልሎች የኮንስትራክሽን አገልግሎት በመስጠት ዘርፉን ማሳደግና የህዝቡን የልማት ፍላጐት ማርካት፣

1. To transform the sector by carrying out building works and providing construction services within the Region and the neighboring regions beyond as well as to satisfy the developmental needs of the people;

2. ወጭ ቆጣቢ የግንባታ ግብአቶችን በማምረት፣ በማስመረት ወይም እንዳስፈላጊነቱ ከውጭ በማስገባት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ወይም እነዚሁኑ ምርቶች በግንባታ ተግባር ለተሰማሩ ሌሎች የመንግስትም ሆኑ የግል ተቋማት በማቅረብ

2. To cause the utilization of low-cost construction inputs by producing or cause the production or, when deemed necessary, importation of same, or to

የግንባታ ግብአቶችን እጥረት ማቃለል።

alleviate the shortage of construction inputs by supplying such inputs to other governmental or private institutions engaged in the construction works.

7. የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት

1. የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት በባህር ዳር ከተማ ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ የሚቋቋሙ ቅርንጫፍና የኘሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል።

7. Head Office of the Enterprise

1. The head office of the Enterprise shall be in the city of Bahir Dar.
2. Without prejudice to the provision of Sub Art. (1) of this Article hereof, the Enterprise may have branch and project coordinating offices to be established at any place, as deemed necessary.

8. ድርጅታዊ አቋም

ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሰረት ከዚህ በታች የተመለከቱት አካላት ይኖሩታል፦

1. የስራ አመራር ቦርድ፣
2. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ዋና ስራ አስኪያጅና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ስራ አስኪያጅ/ ስራ አስኪያጆች፣
3. ለስራው የሚያስፈልጉ ሌሎች የበታች ክፍሎችና ደጋፊ ሰራተኞች።

8. Organizational Status

The Enterprise shall, pursuant to this Regulation, have organs indicated here below:-

1. Board of Management;
2. A general manager and Deputy General Manager/ Managers to be appointed by the Head of the Regional Government, as may be necessary;
3. Other lower divisions and support staff necessary for the work.

ክፍል ሦስት

ስለድርጅቱ ስልጣንና ተግባር

PART THREE

POWERS AND DUTIES OF THE ENTERPRISE

9. ስልጣንና ተግባር

ድርጅቱ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በክልሉ እና ከክልሉ ውጭ የሚከናወኑትን የመንግስት፣ የግልም ሆነ የማህበራት ግንባታ ስራዎች ያከናውናል፣
2. የገበያ አዋጭነትን በየጊዜው እያጠና በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የግንባታ ሥራዎችን ሊያከናውን ይችላል፤ ለንዑስ ተቋራጮች የሚሰጣቸውን የግንባታ ውሎች በተመለከተ የሱፐርቪዥንና ወይም ፍላጎቱ ላላቸው ሌሎች ወገኖች የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አገልግሎቶችን ይሰጣል፣
3. ለስራው የሚያስፈልጉትን ማሽነሪዎች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ግብአቶች ከውጭ ያስመጣል፣ ይጠቀማል፣
4. ለተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች የተሟላ የጥገና፣ የመለዋወጫ አቅርቦትና አስተዳደር ሥራዎችን ይፈፅማል፣
5. ለኮንስትራክሽን አገልግሎት የሚውሉ የአካባቢ ግብአቶችን ያመርታል፣ ያስመርታል፣ ይጠቀማል፣ ይሸጣል፣
6. ኢኮኖሚያዊ የሆነና በገበያ ህግጋት ላይ የተመሰረተ ስልት በመጠቀም ልዩ ልዩ መረጃዎችን ይተነትናል፣ የድርጅቱን የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ፣ የማሽነሪና የተሽከርካሪ አጠቃቀም

9. Powers and Duties

The Enterprise shall, pursuant to this Regulation, have the following specific powers and duties:-

1. Carry out such construction projects as are undertaken by the government, the private sector and cooperatives inside and outside the Region;
2. Possibly carry out building works in all parts of the country by periodically conducting market feasibility studies and render supervision and construction management services with regard to either construction contracts given out for sub contractors and/or those parties in need of same;
3. Import and utilize those machineries, vehicles and other related inputs necessary for the work;
4. Perform a full-fledged maintenance, spare parts' delivery and administrative activities in relation to vehicles and machineries;
5. Produce local inputs that may be used for construction services, have same produced, utilize or sell thereof;
6. Using a mechanism which is economical and founded on marketing rules; analyze various data, as well as

ፖሊሲዎችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

initiate the man power, financial, machinery and vehicle utilization policies of the Enterprise and implement same upon approval;

7. ዓላማዎቹን ለማስፈፀም አመቺ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ይቀዳል፣ ያላምዳል፣ ይጠቀማል፣ አጠቃቀሙን በተመለከተ ጥናትና ምርምሮችን ያደርጋል፣ ከምርምር ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል፣ ጠቃሚ የምርምር ውጤቶችን በስራ ላይ ያውላል፣

7. Emulate, adapt and employ technologies that are suitable for the realization of its objectives; conduct researches regarding the utilization of such technologies; work in unison with the research institutions and implement useful research findings thereof;

8. እንደ አስፈላጊነቱ በዘርፉ ከተሰማሩ ብሄራዊና አለምአቀፋዊ የስራ ተቋራጮች ጋር በመተባበርና በሽርክና ይሰራል፣

8. When necessary, work in cooperation and partnership with the national and global contractors engaged in the sector;

9. ሀንፃዎችን እየገነባ እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች በኪራይም ሆነ በሽያጭ በማስተላለፍ ገቢዎችን ያመነጫል፣ ለተመሳሳይ ልማት ያውላል፣

9. Generate revenues by constructing buildings and, as deemed necessary, by passing them on to beneficiaries either through rent or sale as well as employ same for similar developmental efforts;

10. ለግንባታ የሚያስፈልጉትን ወጭ ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎች ለመቅዳት፣ ለማላመድ፣ ለማምረትና ጥራታቸውን ለመፈተሽ የሚያስችሉ ተቋማት እንዲፈጠሩ አስፈላጊውን ልምድ ያሰባስባል፣ ይህንኑ ለስራ አመራር ቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድለትም ያቋቁማል፣ ይመራል፣

10. Gather the experience necessary for the creation of institutions that would enable to emulate, adapt, produce and inspect the quality of the low-cost technologies essential for construction, submit same to the board of management as well as establish and manage same upon

11. ተሽከርካሪዎችንና ሌሎች የኮንስትራክሽን መሳሪያዎችን እንደአስፈላጊነቱ ያከራያል፣

11. Rent out vehicles and other construction machineries, as may be necessary;

12. ለተቀናጀ የቤቶች ልማት እንቅስቃሴ አወንታዊ አስተዋፅኦ ያላቸውና ለተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችም ሆነ ለግለሰቦች አገልግሎቶች ሊውሉ የሚችሉ ሕንፃዎችን ይገነባል፣

12. Construct buildings having a positive contribution for the integrated housing development program and capable of addressing the needs of the various governmental and non-governmental organizations as well as private persons;

13. ግንባታውን ለማከናወን የሚያስፈልገው የፋይናንስ አቅርቦት የሚገኝባቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻል፣

13. Facilitate the conditions through which the financial resources necessary to carry out the construction may be obtained;

14. የህንፃ ማከፋፈያ ግድግዳዎችን በማምረትና ለተጠቃሚዎች በማቅረብ ወጭ ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን ተጠቅሞ የዘርፉን ፍላጐቶች ያሟላል፣

14. Meet with the demands of the sector by producing wall partitions of buildings and supplying same for clients using low-cost technologies;

15. የክልሉን የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት በማድረግ አላማዎቹን ያሳካሉ ተብለው በሚታሰቡ ሌሎች ተግባራት ላይ ይሰማራል፣

15. Engage in such other tasks as are supposed to attain its objectives based on the priority directions of the Region;

16. ከሌሎች ተቋማት ጋር ሽርክና በመመስረትና ባለ አክሲዮን በመሆን ራሱን ለማጠናከር ይጥራል፣

16. Strengthen itself by partnering with other institutions and becoming share holder thereof;

17. አላማዎቹን ለማሳካት ይቻለው ዘንድ ተፈላጊ አደረጃጀቶችን እያጠና ለስራ አመራር ቦርዱ በማቅረብ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፣

17. Study the required structures with a view to facilitating the accomplishment of its objectives, propose same to the board of

18. በህግ መሰረት ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

18. Enter into contracts in accordance with law, own property, sue or be sued in its own name;

19. ዓላማዎቹን ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

19. Perform such other related activities as may be necessary for the attainment of its objectives.

10. ስለ ስራ አመራር ቦርድ መቋቋምና ተጠሪነት

10. Establishment and Accountability of the Board of Management

1. የድርጅቱን ስራዎች በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር የስራ አመራር ቦርድ ከዚህ በኋላ "ቦርዱ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

1. There is hereby established, as per this regulation, a board of management /hereinafter referred to as **"the Board"**/ capable of directing and coordinating over the activities of the enterprise.

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይሆናል።

2. The board shall be accountable to the Head of the Regional Government.

11. ስለ ቦርዱ የአባላት ጥንቅርና የአገልግሎት ዘመን

11. Membership Composition and Term of Office of the Board

1. ቦርዱ በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየሙና ሰብሳቢውን ጨምሮ ከ 5 እስከ 7 የሚደርሱ አባላት ይኖሩታል።

1. The board shall have members designated by the Head of the Government numbering from 5 through 7, including the

2. የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል።

3. የቦርዱ አባላት የአገልግሎት ዘመን ሦስት አመት ይሆናል። ሆኖም ለተጨማሪ አንድ የአገልግሎት ዘመን በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ።

4. የቦርዱ አባላት ጥቅማ ጥቅም በድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ተጠንቶ በቦርዱ አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ ይወሰናል።

2. The general manager of the enterprise shall serve in the capacity of a secretary of the board without having the right to vote.

3. The term of office of the board members shall last three years; provided, however, that they may be reelected for one additional term;

4. The allowance of the Board Members shall, having been studied by the general manager of the Enterprise and obtained the opinion of the board, be submitted to and determined by the Council of the Regional Government.

12. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር

ቦርዱ በዚህ ደንብ መሰረት የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ድርጅቱ የሚመራበትን አጠቃላይ ፖሊሲ በማመንጨት ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፣ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፣

2. የድርጅቱን የሥራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቆች መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን በቅርብ ይከታተላል፣

12. Powers and Duties of the Board

The board shall, pursuant to this regulation, have the following specific powers and duties:-

1. Initiate the general policy in which the Enterprise may be directed and submit same to the Council of the Regional Government as well as have it approved and follow up its implementation thereof;

2. Examine and approve the draft work program and executionary budget proposal of the Enterprise and closely follow up its implementation

3. ድርጅቱ በሰው ኃይል፣ በመሳሪያና በስራ አመራር ረገድ የሚጠናከርበትን መንገድ ያስጠናል፣ ጥናቱንም ጠቃሚ ሆኖ ሲያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

3. Cause the study of ways through which the Enterprise might become strengthened in-terms of manpower, equipment and management as well as cause the implementation of such study when so found useful;

4. የድርጅቱ ሃብትና ንብረት በአግባቡ መያዙንና የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አላማዎች ለማሳካት መዋሉን ያረጋግጣል፣

4. Ensure that the resource and property of the Enterprise is properly handled and utilized for the realization of the Region's social and economic objectives;

5. ይህንን ደንብ መሰረት በማድረግ ድርጅቱ በተግባር ላይ የሚያውላቸውን የተለያዩ መመሪያዎች ያወጣል፣

5. Issue various directives to be implemented on the part of the Enterprise in accordance of this Regulation;

6. ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል።

6. Submit periodic reports to the Head and the Council of the Regional Government.

13. የቦርዱ የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርዓት

13. Meeting Time and Decision-Making Procedure of the Board

1. ቦርዱ በ 3 ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያካሂዳል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ከዚህ ባነሰ ጊዜ ውስጥ ከማድረግ አይታገድም።

1. The board shall convene its regular meeting once in three months; it may, however, not be barred from holding extraordinary meetings at any time below what has been prescribed hereof, as deemed necessary.

2. ከቦርዱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ-ጉባኤ ይሆናል።

2. There shall be a quorum where more than half of its members are present

3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ። ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

4. ከዚህ በላይ የሰፈሩት የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ስነ-ስርአት ማስፈፀሚያ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

3. The decisions of the board shall be passed by majority vote; in case of a tie, however, the chairperson shall have a casting vote.

4. Without prejudice to the aforementioned provisions of this Article hereof, the board may issue its own meeting time and decision-making procedure implementing directive.

14. ስለ ዋና ስራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

1. የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ በቦርዱ አቅራቢነት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ሆኖ በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 ስር ለድርጅቱ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስኪያጁ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ የድርጅቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

14. Powers and Duties of the General Manager

1. The general manager of the Enterprise shall, having been appointed by the Head of the Regional Government upon his presentation by the board, execute the powers and duties vested in the Enterprise pursuant to Art. 9 of this Regulation hereof.

2. Without prejudice to the general provision laid down under Sub-Art. (1) of this Article hereof, the general manager shall have the powers and duties specified here below:-

a) Direct, coordinate and supervise over the day to day activities of

the Enterprise;

ለ/ የድርጅቱን የስራ ክፍሎች ያዋቅራል፣ የሰራተኞችን ደመወዝና አበል እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

b) Organize the work divisions of the Enterprise as well as prepare the salary and allowance of employees, submit it to the Board and implement same upon approval;

ሐ/ በድርጅቱ ስም የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ሂሳቡ በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፣

c) Open and operate a bank account in the name of the Enterprise as well as ensure that its books of account are kept properly;

መ/ የድርጅቱን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና የስራ ፕሮግራም እያዘጋጀ ለቦርዱ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም በተግባር ላይ ያውላል፣

d) Prepare short, medium and long term plan and work program of the Enterprise, submit it to the Board and implement same upon approval;

ሠ/ ተጠሪነታቸው ለዋና ስራ አስኪያጁ የሆኑትን የበታች ስራ ኃላፊዎች ቅጥር፣ ምደባና ስንብት ለቦርዱ አቅርቦ ያስፀድቃል፣

e) Submit to and have the recruitment, assignment and dismissal of those division heads whose accountability is to and whose rank is below the general manager, approved by the Board;

ረ/ ለድርጅቱ በተፈቀደለት የስራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣ በስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

f) Cause the disbursement of money in accordance with the work program approved for the Enterprise and thereby supervise over its implementation thereof;

ሰ/ ይህንን ደንብ መሰረት አድርገው በቦርዱ የሚወጡትን መመሪያዎችና የሚተላለፉትን ውሳኔዎች ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣

g) Implement as well as cause the implementation of those directives issued and decisions passed by the Board in pursuance

ሸ/ ድርጅቱ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚገኘው ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብና በአግባቡ እንዲያዝ ያደርጋል፣

ቀ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ድርጅቱን ይወክላል፣

በ/ ለቦርዱና ለርዕሰ መስተዳድሩ ወቅታዊ የስራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶችን ያቀርባል፣

ተ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

h) Cause the timely collection and proper handling of the revenue that may be generated from the services provided by the Enterprise;

i) Represent the Enterprise in its dealings with third parties;

j) Submit periodic performance and financial reports to the Board and the Head of Government;

k) Perform such other related duties as may be assigned to him by the Board.

15. የምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ ስልጣንና ተግባር

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የዋና ስራ አስኪያጁን አሿሿም በሚመለከት የሰፈረው ድንጋጌ ለምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናል።

2. የምክትል ዋና ስራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለዋና ስራ አስኪያጁ ሆኖ፥-

ሀ/ በዋና ሥራ አስኪያጁ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

15. Powers and Duties of the Deputy General Manager

1. The provision laid down under Art. 14 Sub-Art. (1) of this Regulation hereof regarding the appointment of the general manager shall, mutatis mutandis, apply to that of the deputy general manager.

2. Having been accountable to the General Manager of the Enterprise, the deputy general manager shall:-

a) Carry out such duties as may be assigned to him by the general manager;

ለ/ ዋና ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል።

b) Act on behalf of the general manager in the absence of the former or under the circumstances where and when he is unable to perform his duties.

16. ስለ ሰው ኃይል ቅጥርና አስተዳደር

1. የድርጅቱ ሰራተኞች ቅጥርና አስተዳደር በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ህግ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጅቱ እንደአስፈላጊነቱ የራሱን የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ይኸው ለቦርዱ ቀርቦ ሲፀድቅም በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

16. Recruitment and Administration of the Man Power

1. The recruitment and administration of employees of the Enterprise shall be executed in accordance with the Labor Laws.

2. Without prejudice to the provision stipulated under Sub-Art. (1) of this Article hereof, the Enterprise shall, as deemed necessary, prepare its own man power administration directive, submit to and cause the implementation of same upon approval by the Board.

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART FOUR

MISCELLANEOUS PROVISIONS

17. ስለ ድርጅቱ በጀት አመት

የድርጅቱ የበጀት አመት የክልሉ መንግስት የሚሰራበት የበጀት አመት ይሆናል።

17. Budget Year of the Enterprise

The budget year applicable by the Enterprise shall be that of the Regional Government.

18. ስለሂሳብ መዛግብት

1. ድርጅቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል።

2. የድርጅቱን የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች አያያዝ በተመለከተ በቦርዱ ተቀባይነት ያላቸው የሂሳብ አሰራሮች በስራ ላይ እንዲውሉ ሊደረግ ይችላል። ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

18. Books of Account

1. The Enterprise shall keep complete and accurate books of account.

2. With regard to the keeping of books of account and financial or property related documents of the Enterprise, the accounting procedures acceptable on the part of the Board may be made operational; particulars shall be determined by a directive to be issued following this Regulation.

19. ስለሂሳብ ምርመራ

የድርጅቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በየአመቱ ይመረመራሉ።

19. Auditing

The books of account and financial as well as property related documents of the Enterprise shall be annually audited by those external auditors to be designated by the Board.

20. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በደንብ ቁጥር 83/2003 ዓ.ም ተቋቁሞ የነበረው የአማራ ክልል ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ አዲስ ወደ ተቋቋመው ድርጅት ተላልፈዋል።

20. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Amhara Region Construction and Housing Development Agency established by Regulation No. 83/2011 are hereby transferred to the Enterprise which is newly established under this Regulation.

21. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለ ማይኖራቸው ሕጐች

21. Repealed and Inapplicable Laws

1. የአማራ ክልል ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 83/2003 ዓ.ም ተሽሮ በዚህ ደንብ ተተክቷል።

2. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

22. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ቦርዱ ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

23. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
መጋቢት **25** ቀን **2007** ዓ.ም
ገዱ አንዳርጋቸው
የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ርዕሰ-መስተዳድር

1. The Amhara Region Construction and Housing Development Agency Establishment, Council of Regional Government Regulation No. 83/2011 is hereby repealed and replaced by this Regulation.

2. No other regulation, directive or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this regulation, be applicable in respect of matters covered therein.

22. Power to Issue Directives

The Board may issue directives necessary for the full implementation of this Regulation.

23. Effective Date

This regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 3rd day of April, 2015
Gedu Andargachew
Head of Government of the
Amhara National Regional State